# ሐገር በቀል ዕይታ ለኢትዮጵያ ግብርና


## ፀደቀ አባተ

*መሥራች እና መሪ*

ሐገር በቀል ዕይታ (Homegrown Vision)

www.homegrownvision.org



ጥቅምት 27 2012 በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ እና በሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ትብብር የቀረበ ገለፃ


## ማጠቃለያ ሐሳብ (Abstract)


ኢትዮጵያ ሐገራችን ለሺ ዘመናት የቆየ የግብርና ታሪክ አላት፤ ማረሻ መጠቀም የጀመርነው ከ500 ዓመተ ምሕረት በፊት እንደሆነ የታሪክ መረጃዎች ያሳዩናል። ባለፉት 60 ዓመታት የነበሩ የአገዛዝ ሥርአቶች የኢትዮጵያን ግብርና ለማዘመን የየበኩላቸውን ድርሻ አበርክተዋል። ከፍተኛ የግብርና ትምሕርት ተቋማትን መገንባትን፤ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማሳደግን፤ ዘመናይ ቴክኖሎጂዎችን ማውጣትን እና ማስረፅን እንደ ዋቢ ያቀርቧል። እኤአ በ1970ዎቹ የቡና ኢንዱስትሪን ከቡና ፍሬ በሽታ መታደግ፤ እኤአ በ1970ዎቹ እና በ1980ዎቹ የተለያዩ የጥራጥሬ፣ የአትክልት እና የፍራፍሬ ተክሎችን ማስተዋወቅ፤ እኤአ በ1990ዎቹ የዲቃላ በቆሎን ቴክኖሎጂ በሐገር ውስጥ ማፍለቅ እና ፤ እኤአ በ2000ዎቹ ደግሞ ያሉትን ቴክኖሎጂዎች ለአርሶ አደሩ ለማዳረስ የተደረጉ ጥረቶች በነኚህ ጊዚያት የተከናወኑ የመልካም ሥራ ውጤት ምሳሌዎች ናቸው።

እስካሁን በተደረገው የምርምር እና ልማት ጉዞ በተለይ በብርእ እና አገዳ  እንዲሁም በጥራጥሬ ሰብሎች ሻል ያሉ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በሥራሥር (ምናልባት ከድንች በስተቀር)፤ በቅባት ሰብሎች፤ እና በእንስሳት ሐብት ይህ ነው የሚባል ውጤት ለማስመዝገብ አልተቻለም። ለዚህ ሁኔታ በዋናነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች አንዱ ለብርዕ እና አገዳ ሰብሎች ከዚያም የውጭ ምንዛሪ ለሚያስገኙ ጥራጥሬ ሰብሎች የተሰጠው ሚዛናዊ ያልሆነ የምርምር እና ልማት ትኩረት ነው። እንዲህ ዓነቱ አካሄድ በኛ ሐገር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን እኤአ በ1960ዎቹ መጨረሻ እና በ1970ዎቹ በእስያ እና በላቲን አሜሪካ የተከሰተውን "አረንጓዴ አብዮት" ለመኮረጅ እና በአፍሪቃ ውስጥ ለማስፋፋት የተደረገ ሙከራን ተከትሎ የመጣ ዘይቤ ነው። እንደ እንሰት፣ ጎመንዘር፣ ሐበሻ ሱፍ፣ ኑግ፣ እና ለመሳሰሉ ሐገርበቀል እና ለምግብ ዋስትና፣ ለውጭ ምንዛሪ፣ ለፋብሪካዎች ጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ ከውጭ ለሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች መተኪያ፣ አልፎም የአካባቢን ደህንነት በመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላላቸው ሰብሎች የምርምር እና ልማት ትኩረት ባለመስጠታችን ብዙ ዋጋ እየከፈልን እንገኛለን።

እስካሁን የታዩ ጥሩ ውጤቶችም ቢሆኑ ቀጣይነት ሊኖራቸው እንደማይችል ምልክቶች እየታዩ ነው። የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት እያደገ የመሄዱን ያህል በአንፃሩ የነፍስወከፍ የርሻ መሬት እየጠበበ መምጣቱ የግብርናን አትራፊነት ከጥያቄ ውስጥ ከትቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የብዙዎቹ ሰብሎች (ምሳሌ፡ ቡና) መርታማነት እየቀነሰ መጥቷል። በዚያው መጠን ወደ ውጭ የምንልከው መጠን እና የምናገኘው ገቢ ባንድ በኩል ሲያሽቆለቁል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ የምናስገባው መጠን እና

ወጭ እየናረ ሄዷል። ለምሳሌ ያህል ባጠቃላይ ከቅባት ሰብሎት ውጭ ንግድ የምናገኘው ገቢ ተደምሮ ለምግብ ዘይት መግዣ ብቻ የምናወጣውን ወጭ እንኳ አይሸፍንም (የአሜርካን ዶላር 556 ሚሊዮን ከ588 ሚሊዮን ዓመታዊ ወጭ ጋር ያነፃፅሯል)። ሌላው ዓለም ባለፉት ሃያ እና አርባ ዓመታት የሰብሎችን ስብጥር በማሻሻል እና አማራጮችን በማቅረብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ እና የካባቢ ደኅንነት ፋይዳዎችን እየተቀዳጀ ይገኛል።

በሽመታም ሆነ በእርዳታ ከውጭ  የምናስገባው የምግብ መጠን እንዳለ ሆኖ፣ የሐገር ውስጥ ምርት ሲያድግ የቆየው እና ሕዝቡን ለመመገብ የተቻለው ባመዛኙ ጫየካዎች እና ቁጥቋጦችን በመመንጠር እና የመሬቱን የቆዳ ስፋት በመጨመር ነበር። ካሁን ወዲያ ግን በአርሶ አደሩ አቅም ለመስፋፋት ያለው ዕድል እጅግ የጠበበ ነው፤ አርሶ አደሩ ሊያደርግ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል። ከዛሬ 30 ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ወደ 191 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። ይህ ማለት ደግሞ ምርት እና ምርታማነታችን አሁን ካለበት በእጥፍ መጨመር ይኖርበታል ማለት ነው። ካለፉት 60 ዓመታት ያገኘነው ልምድ እንደሚያሳየን ነፍስወከፍ የርሻ መሬት ካንድ ሄክታር በታች በሆነበት፤ የማዳበሪያ አጠቃቀም ከሚሰጠው ምክረሐሳብ ከግማሽ ዝቅ ባለበት፤ የምርጥዘር አጠቃቀም ሽፋን ከ10% በታች በሆነበት፤ የፀረአረም፣ ፀረበሽታ፣ እና ፀረተባይ ሽፋን 20% በሆነበት፤ የቴክኖሎጂ ስርፀት ሽፋን ከ24% በታች በሆነበት፤ እና የመስኖ አጠቃቀም ወደ1% አካባቢ ባለበት ሁኔታ፣ ከላይ ከተጠሰው ግብ መድረስ አዳጋች ይሆናል።

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር እና ልማት ገቺ ጉዳዮች በቴክኒክ ላይ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም። እንዲያውም ተቋማዊ ተግዳሮቶች የበለጠ ሚና እንደሚጫወቱ ካገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ያገኘነው ልምድ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ከነኚህ መካከል ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው ይጠቅሷል፡-

ሀ) ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ተዋፅኦቻችን (ምናልባት ከቆዳ ውጤቶች እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከፊልም ቢሆን የፍየል ሥጋ በስተቀር) የሚላኩት የዋጋ እሴት ሳይጨመር በጥሬው ነው፤

ለ) የተቋማት አስተዳደር (Governance)ን ጉዳይ የተመለከትን እንደሆነ፣ ለምሳሌ ያህል የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እኤአ በ1966 ዓም በአዋጅ ሲቋቋም ከፊል ራስገዝ ሙብት ስለነበረው በተለይ በመጀመሪያዎቹ አራት አሥርት ዓመታት በርካታ ለሐገር የሚጠቅሙ አኩሪ ውጤቶችን ለማስመዝገብ ችሏል፤ ዛሬም ቢሆን እየተንቀሳቀሰ ያለው ከዚያን ጊዜ ከነበረው ጠንካራ መሠረት ሲንከባለል በመጣው መንፈስ ነው ማለት ይቻላል። ውሎ አድሮ ግን የነበረው ሥልጣን እና ሐላፊነት እየተሸረሸረ በመሄዱ እና ኃላፊነት ላይ የሚመደቡ ግለሰቦችም ሙሉ ሥልጣናቸውን ሥራ ላይ እንዳያውሉ የተገደቡ (Empowered ያልሆኑ) በመሆናቸው መ/ቤቱ የተጣለበትን ግዴታ በተፈለገው ስልጠት ለመወጣት ያለውን አቅም ውሱን አድርጎታል፤

ሐ) የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ሥርዓትን የሚያስተባብር ጠንካራ አካል መኖር እንዳለበት የታመነ ቢሆንም እስካሁን ሥራ ላይ አልዋለም፤ በፌደራል እና ክልል ተቋማት፣ በፌደራል እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ያለው የሥራ ድርሻ እና ኃላፊነት ባለመለየቱ ድግግሞሽ እና የንብረት ብክነት ይታያል፤

መ) የኃላፊነት ቦታ ምደባ ባመዛኙ ብቃትን፣ ችሎታን፣ እና ልምድን መሰሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ሐገሪቱ ልታገኝ የሚገባትን አስተዋፅኦ ገድቦታል፣ አልፎ ተርፎም ለከፍተኛ ኪሣራ የተዳረግንባቸው አጋጣሚዎችም ነበሩ፤

ሠ) ካለፉት አሥር ዓመታት በላይ የኢትዮጵያ ግብርናን ለማዘመን በመንግሥት በኩል ከፍተኛ እና ልዩ ጥረት ተደርጓል፣ ዓላማው የተቀደሰ ሆኖ ሳለ  አጀማመሩ እና አተገባበሩ ላይ ችግር ስለነበረበት ግቡን ሊመታ አልቻለም፣ ቀድሞውንም ሲጀመር ጥልቀት ባለው እና ሁላቀፍ ጥናት ላይ የተመሠረተ አልነበረም፤ ዕውቀት እና ሰፊ ልምድ ያላቸው እትዮጵያውያን ባለሙያዎች የተሳተፉበት፣ የተወያዩበት ሳይሆን ከላይ ወደታች ዓይነት አሠራር ነበረበት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ከዚህ ልምድ በቂ ትምህርት አግኝተውበታል የሚል ተስፋ አለኝ።

የወደፊት ጉዟችንን በተመለከተ አሁን ዝርዝር ውስጥ መግባት አስፈላጊ መስሎ አይታየኝም። ባጠቃላይ ግን መንግሥት በክህሎታቸው፣ በሙያቸው፣ እና በስብዕናቸው አክብሮትን የተላበሱ ባለሙያዎችን ያካተተ፣ ተጠሪነቱ የሐገሪቱ የመጨረሻ ሥልጣን አካል ቢሮ የሆነ፣ ልዩ ከፍተኛ ግብረኃይል እንዲያቋቁም እና ግብረኃይሉም የኢትዮጵያ ግብርና ዋና ዕቅድ (Master Plan) አውጥቶ ለሐገራዊ ውይይት (National Dialogue) እንዲያቀርብ፣ ሁሉም የመከረበት እና ከስምምነት (Consensus) ላይ የደረሰበት ጉዳይ ወደ ሥራ እንዲተረጎም ያስፈልጋል። ይህ ማለት እንግዲህ የሚፈለገው ለውጥ ጥገናዊ ሳይሆን መሠረታዊ (ሰብሮ መውጣት የሚያስችል)፤ የምንጓዝበት መንገድ አቋራጭ ሳይሆን ሰቅ ጠበቅ አድርጎ አስሮ ረዥም ጉዞ የሚኬድበት፣ ለኢትዮጵያ ችግር መፍቻ ቁልፉ ያለው ኢትዮጵያውያን ዘንድ መሆኑ ታውቆ፣ ለተውሶ ሳይሆን ለሐገርበቀል መፍትሔዎች ቅድሚያ የሚሰጥበትን ሁኔታ መፍጠር ማለት ነው።